# በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ማዕ/ጎ/ሀ/ስ ለደብረ ኀይል ወደብረ ጥበብ በአታ ለማርያም ካቴድራል ሰንበት ትምህርት ቤት የተሰጠ

## የመንፈሳዊ የንግግር ጥበብ ኮርስ

## ክፍል 1




**አዘጋጅ፦ በትረ ማርያም አበባው ካሣ**

**(የመጻሕፍተ ሊቃውንት፣ የመጻሕፍተ ብሉያትና የመጻሕፍተ መነኰሳት ትርጓሜ መምህር)**

**ሐምሌ ፳፯፣ ፳፻፲፫ ዓ.ም**

# መንፈሳዊ የንግግር ጥበብ
## Spiritual Rhetoric

የንግግር ጥበብ ሐሳብን ለሰሚው በሚስብ መልኩ የማቅረብ ጥበብ ነው፡፡ መንፈሳዊ የንግግር ጥበብ የሚባለው ሰሚውን ለመጥቀም የሚደረግ የትምህርት፣ የምዕዳን፣ የምክር፣ የተግሣጽ ንግግር ነው፡፡ ዓላማው ሰዎችን መጥቀም ስለሆነ የሰዎችን ስሜት የሚጎዳ ለጸብ የሚያነሳሳ መሆን የለበትም፡፡ ከዚያ ይልቅ የተጎዱትን የሚያበርድ፣ ያዘኑትን የሚያረጋጋ መሆን ይገባዋል፡፡ አንደበት የተፈጠረው እግዚአብሔርን ለማመስገንበትና ሌላውን ለመጥቀምበት ነውና፡፡ መንፈሳዊ የንግግር ጥበብ መሠረቱ ፍቅር ነው፡፡ "ነገር አዋቂ አንደበት ወንድሜ ወንድሜ ማለትን ያበዛል፤ በጎ አንደበት ወዳጆችን ያበዛል" እንዲል (ሲራ. 6÷5)፡፡ ለሌሎች እንደሚጠቅም ለመግለጽም "መፈወሱ ለሳን ዕፀ ሕይወት ውእቱ" ይላል (ምሳ.17÷4)፡፡ መንፈሳዊ የንግግር ጥበብ ሌሎችን የምናንጽበት፣ የእግዚአብሔርን ሥራ የምንገልጽበት ነው፡፡ መልካም ንግግር ሕይወት ሲሆን ክፉ ንግግር ሞት ነው፡፡ "ሞት ወሕይወት ውስተ እደ ልሳን" እንዲል (ምሳ.18÷21)፡፡ በጎ ንግግር ሰውን ጆሮ እንደሚያሰኝም "በጎ አንደበት ጆሮ ያሰኛል" ይላል (ሲራ.40÷

የክፉ ሰው ንግግር ግን አጥንት ይሰብራል (ሲራ.28÷17)። መንፈሳዊ የንግግር ጥበብን ከመጽሐፍ ቅዱስ እንማራለን። ከምንም በላይ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው ንግግር ቀና መሠረታችን ነው። ስለ ክርስቶስ ወንጌላዊው ሉቃስ "ወእለ ሰምዕዎ ኵሎሙ ያንክሩ ሞገሰ ቃሉ ወሠዐሠዐ አፉሁ" ብሏል (ሉቃ.4÷22)። ለመንፈሳዊ የንግግር ጥበብ ውስጥ መሠረታዊ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው።

፩. ሞገሰ ቃል (የቃል መወደድ)

፪. ጣዕመ ነገር (የነገር ጣዕም)

፫. ሠዐሠዐ አፉ (የአንደበት ቅልጥፍና)

ጣዕመ ነገር የሚባለው የሐሳቦችን ፍሬ ነገር ነው። ሞገሰ ቃል ደግሞ ፍሬ ሐሳብ የምናስተላልፍበት ቃል መወደድ ነው። ሠዐሠዐ አፉ እጅግም ሳይዘገይ እጅግም ሳይፈጥን መካከለኛ በሆነ መለኪያ ለሰሚ ግልጽ በሆነ መልኩ ንግግርን ማቅረብ ነው።

## የመንፈሳዊ ንግግር ጥበብ መርሆዎች

፩. ማወቅ፦ ልንናገረው ስለምንሰብከው ነገር ግንዛቤ ካለን ንግግራችን ግልጽ ይሆንና ሰሚን የሚያስደስት ይሆናል። ስለዚህ ለጀመርነው ጉዳዩን በደንብ ማወቅ ይገባናል።

፪. የቋንቋ ዕውቀት መኖር፦ ምንም እንኳ ስለአንድ ነገር ግንዛቤ ቢኖረንም ያንን የተገነዘብነውን ነገር ለሌሎች ሰዎች ለመግለጽና ለማብራራት የቋንቋ ዕውቀት አስፈላጊ ነው።

፲. የሰሚን ዕድሜ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ማሕበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዝንባሌ መለየት።

፲፩. የንግግሩን ዓላማ መለየት (የመንፈሳዊ ንግግር ዋና ዓላማ የእግዚአብሔርን ዕውነት መመስከርና ሰዎችን መጥቀም ነው)።

፲፪. ንግግሬችንን ቅደም ተከተል ማስያዝ፡-

- መግቢያ (የሰማዕያንን ትኩረት የሚስብ ኃይለ ቃል፣ ንድፍ ወይም ጉዳይ ማቅረብ)
- መካከል፡- ንግግሬችንን በምሳሌዎች፣ በታሪኮችና ለመሳሰሉ መንገዶች ከፋፍሎ ማቅረብ
- ማጠቃለያ፡- ዋናውን መልእክት ከዕለት ሕይወት ጋር አቀናጅቶ አጭር መግለጽ።

፲፫. ምሳሌዎችንና ታሪኮችን መጠቀም። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር በእርሻ፣ በእርሻ፣ በእረኞችና ለመሳሰሉት እየመሰለ ያስተምር ነበር።

፲፬. አይታችንን ሁሉን ያማከለ ማድረግ (ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ አለማየት፣ ፈገግታ ያልተለየው ገጽ መኖር፣ የአካል እንቅስቃሴያችንና ንግግሬችን ማቀናጀት)።

፲፭. መለማመድ፡- ብዙ ሰዎች ጥሩ ተናጋሪ የሆኑት ለልምምድ፣ ለልመማር፣ ለማንበብና ለማሰላሰል ነው። በተማሪነቱ ጊዜ ጌታን ከሰማይ እሳት አውርደን ሰዎችን እንዲያጠፋ የጠየቀ ዮሐንስ ከተማረ በኋላ ግን ሮምናን ለማዳን በእሳት አንዳጅነት እስከ ማገልገል ደርሷል። ትምህርት አመለካከትን፣ አነጋገርን ይለውጣል

፱. ዝግጅት ማድረግ፡- ይህ ዝግጅት ዘርፈ ብዙ ነው። ከምናደርጋቸው ዝግጅቶች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ።

- ስለምናወራው ነገር በቂ ዕውቀትን ከመጻሕፍት፣ ከሰዎች፣ ከልምዶቻችንና ከመጽሔቶች መሰብሰብ
- እንዴት እንደምታቀርቡት የአነጋገር፣ የእንቅስቃሴ፣ የሰዓት፣ የዓረፍተ ነገር አወቃቀር ዘዴዎችን መለማመድ
- ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን አስቀድሞ መገመትና ሊያጋጥሙ ለሚችሉ ችግሮች ቀድሞ መፍትሔዎችን ማዘጋጀት

፲. ፍርሀትን ማስወገድ፡- የምንናገረው ጉዳይ እስካለ ድረስ ማንንም ሳንፈራ ጉዳዩን መናገርና መግለጽ ይገባናል። ምንም እንኳ ከመድረኩ ለመስማት የተከበሩ ታላላቅ ሰዎች፣ ነገሥታት፣ ጳጳሳት፣ ምሁራን ቢኖሩ ለምናቀርበው ያስከበርነውን ጉዳይ በድፍረት ማቅረብ አለብን። ለምንናገረው ካለው ነገር ላይ ብቻ ትኩረት ማድረግ ይገባናል። ሰዎች ምን ይሉናል በማለት በሰዎች ፍረጃ ላይ የተመሠረተ አቀራረብን ማስወገድ ይገባል።

፲፩. ድግግሞሽንና ተመሳሳይነትን ማስወገድ፡- የሰው ልጆች የተደጋገመ ነገር ብዙ ጊዜ ያሰለቻቸዋል። ስለዚህ የሐሳብ ድግግሞሽን፣ የአቀራረብ ድግግሞሽን ማስወገድ አለብን። አንድ ዓይነት አበቦች ካሉበት ጋሮ ይልቅ የተለያዩ አበቦች ያሉበት ጋሮ ለተመልካቹ ሳቢ ነው። ከተደጋጋሚ ሐሳቦች ይልቅ ያልተደጋገሙ ሐሳቦች ለሰሚው ሳቢ ናቸው።

፲፮. ሐሳብን ማደራጀት፡- ከተበታተኑ ሐሳቦች ይልቅ ለአንድነት ያሉ ሐሳቦች አቅም አላቸው። ከተበታተነ ሐሳብ ይልቅ የተደራጀ ሐሳብ ሰሚውን የመሳብ አቅሙ ከፍተኛ ነው።

፲፯. የድምፀት ስምምነት ማድረግ፡- ሐሳባችንን ለመግለጽ የምንጠቀምባቸውን ቃላትና ዓረፍተ ነገሮች ለትክክለኛ የአነባበብ ስልት ለማንበብ መለማመድ አለብን። አለበለዚያ ማክሰኞ ለማለት ማሳክኞ ብንል እንቸገራለን። ይህ ሁኔታ ደግሞ ሰሚውን ወደ ንቀት ሊያመራው ይችላል። አነጋገራችን እኛን ራሳችንን ሊመስል ይገባል። የሌላ ሰዎችን ድምፀት ለመጠቀም ብለን ችግር ውስጥ መግባት የለብንም። የድምፅ ፍጥነትን እንደ አስፈላጊነቱ መቀያየር። ይህ የሰሚውን ትኩረት ለመሰብሰብ ይጠቅማል።

፲፰. አለመጣደፍ፡- ዝግ ማለትም ሰሚን እንደሚያሰለች ሁሉ መጣደፍም ስናስተላልፈው የፈለግነው ሐሳብ ቀጥታ ወደ ሰሚዎች እንዳይደርስ ያደርጋል። በየንግግራችን መካከል አጭር ዕረፍት ማድረግ ካለብንም ማድረግ ይገባናል።

፲፱. ማወዳደር፣ ማነጻጸር፣ ልዩ ልዩ ዘይቤዎችን መጠቀም፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን መጠቀም፡- ይህ ለምናስተላልፈው መልዕክት ጉልበትን ይሰጠዋል። ለምሳሌ ቅዱሳን አይፈሩም ብለን ከመናገራችን ይልቅ ቅዱሳን እንደ አንበሳ ደፋሮች ስለሆኑ አይፈሩም ብንል ለሰሚው ዘይቤ ተጽዕኖ ፈጣሪነት ከፍ ያለ ነው።

፲፮. በራስ መተማመን፦ ንግግራችንን ለአግባር አዳማ ጉዳዮቻችን እንደምናወራ አድርገን ሳንፈራ ሳናፍር ማቅረብ አለብን:: ስለ ጉዳዩ በቂ ዕውቀት መኖር፣ በቂ ልምምድ ማድረግ በራስ መተማመናችን ላቅ ያደርገዋል።

## የንግግር ክህሎት ጥቅሞች

- እውነትን ለሰሚው በትክክል ተደራሽ ለማድረግ
- ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለንን መልካም ግንኙነት ያጎለብታል:: ይህም ፍቅር ሰላምን ይጨምራል::
- ሌሎች ሰዎችን የማሳመን፣ የመምራት፣ የማነሳሳት አቅምን ይጨምራል:: እነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ትምህርታቸው እስከዛሬ ተወዳጅ የሆነውና የማሳመን አቅማቸው ትልቅ የሆነው ከመንፈስ ቅዱስ ርዳታ በተጨማሪ የንግግር ክህሎትን ተምረው ማወቃቸው ነው።

ንግግራችን ለሰሚው ተወዳጅ ይቀርብ ዘንድ የሰሚውን ፍላጎት፣ ምርጫ፣ ስሜት የሚገልጽ መሆን አለበት:: ከቅዱስ ጳውሎስ የማስተማር ዘዴዎች አንዱ ለአይሁድ እንደ አይሁዳዊ፣ ለአረማውያን እንደ አረማዊ ሆኖ ማስተማሩ ነው። ሌሎችን መሆን ስሜትን መጋራት ነው።

ሌላው በንግግር ጊዜ ልናስተውለው የሚገባን ነገር ሸምድዶ ከማቅረብ ይልቅ ተረድቶ ማቅረብ የተሻለ መሆኑን ነው:: በንግግራችን መካከል መቆራረጥ እንዳይኖር ቁና ቁና ሐሳቦችን የያዘ ትንሽ ማስታወሻ ቢኖረን መልካም ነው:: የምንናገረው ሐሳብ ከሌለን ግን ዝምታ ይሻለናል::